# ኢትዮጵያዊነት፡-

## የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ

# Ethiopiawinnet:

## Council for the Defense of Citizen Rights

## ድርጅታዊ መተዳደሪያ ደንብ (Bylaws)

## ክፍል ፩፡ ራእይ፡ ተልእኮና ዓላማዎች

1. **ኢትዮጵያዊነት** ከፖለቲካ ኃይሎች ገለልተኛና አለማቀፋዊ የሆነ፤በማይገሰሱ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ዙሪያ የተሰባሰቡ የኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ድርጅት ነው። የዚህ ሲቪክ ድርጅት ራእይ "የዜጎች ቃልኪዳን ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ" በሚባለው የመብቶች ድንጋጌ ሰነድ የተዘረዘሩትን መሪ ሃሳቦች የሚያካትቱ ናቸው። ይህ ቻርተር የዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንድ አብይ አካል ነው። የቃልኪዳኑ ራእይ የተመከለው በበለፀገች፣አንድነቷን ባስጠበቀችና ዲሞክራስያዊ ስርዓትን ባቀፈች አዲሲቷ ኢትዮጵያ ነው። ይኸም በሉዓላዊ ዜጎቿ በሚከበረው ታሪካዊ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ነው።

2. **የኢትዮጵያዊነት** ዋና ተልእኮ በአለም አቀፍ ደረጃ የተደነገጉ የዜጎች ሰብዓዊ፡ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መብቶች በኢትዮጵያም እንዲከበሩና እንዲዳብሩ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ነው። በዚህም መሰረት ድርጅቱ የኢትዮጵያውያንን አንድነት መሰረት አድርጎ ከፖለቲካ ተቋማት ጋር ያልተዋቀረ ሰላማዊ፣ህዝባዊና በተለይ ወጣቶችን የሚያሳትፍ አለም-አቀፋዊ የደሞክራሲ ንቅናቄን ኮትኳች ነው። ለዚህ ተግባር ተገቢውን ሁሉ የሚያካትተው አለማቀፋዊዉ ኢትዮጵያዊነት ድርጅት የህዝቡን ሰቆቃ አንገብጋቢነት ግንዛቤ ዉስጥ ላስገባ የዴሞክራሲ ምስረታ ትግል የተባበረና የተቀነባበረ እርምጃን ለመዉሰድ ጠንካራ መሳሪያ ይሆናል ብለን እናምናለን።

3. **የኢትዮጵያዊነት** ዋና አላማዎች ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ያቅፋሉ፡-

   ሀ. የዜጎች ሙሉ መብቶች እንዲጠበቁ፡የህግ የበላይነት እንዲሰፍንና በህግ ፊት የሁሉም ዜጋ እኩልነት እንዲረጋገጥ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ህዝባዊ ድርጅቶች ራሳቸዉን አደራጅተው ዴሞክራሲን ለማስፈን በሚደረገው ትግል ሁሉ በደፋርና ሰላማዊ መንገድ ባለቤታዊ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ የሚቻለዉን እርዳታና ቅስቀሳ ለማድረግ፤

ለ. የወል መለዮዎቻችን ኢትዮጵያዊነትና የአገር አንድነት ከሃይማኖት፡ከጎሳ፡ከጾታ እንዲሁም ከእድሜና ከመደብ ክልል ባሻገር የሆኑ የጋራ መመኪያ መሆናቸውን አስገንዝቢ ተግባራትን ለማከናወን፤

ሐ. የሰዉን ልጅ ማህበራዊ፡ ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች ረገጣን ለመቋቋምና ኢትዮጵያዉያን በሚፈልጉት ሁኔታና ቦታ የመኖር እና የመሥራት መብታቸው እንዲከበርና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጫና ለማድረግ የሚረዱ አለማቀፍ እንቅስቃሴዎችን ለመዘርጋትና ለማጠናከር፤

መ. ኢትዮጵያዉያን ስላለባቸው የዜግነት 'መብትና ግዴታ' ጠንካራ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ በተለያየ መንገድ ለማዎያየት፡ለመማርና ለማስተማር፤

ሰ. የኢትዮጵያን ህዝብ የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን የሚደግፉ የዲፕሎማሲያዊ፡ የፖለቲካና የገንዘብ ርዳታዎች ከአለም-አቀፍ ድርጅቶችና ሀብረሰብ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ በስልት የተቀረጹና የተቀነባበሩ ርምጃዎችን ለመውሰድ፤እንዲሁም

ረ. መንግስትም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤በሃገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሃገር የተደራጁ ወይም የሚደራጁ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያቅፍ ባህል እንዲታነጹና ልምዳቸዉም እንዲአደርጉት የሚቻለዉን ሁሉ ለማድረግ ናቸው።

# ክፍል ፪፡ አወቃቀርና ደንብ

## አንቀጽ 1፡ አደረጃጀት

### 1.1. ስምና ቢሮ

ሀ. የድርጅቱ ስም **"ኢትዮጵያዊነት፡ የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ"** ይሆናል። በአጭር ስም ደግሞ "ኢትዮጵያዊነት" በመባል ሊጠራ ይችላል።

ለ. ኢትዮጵያዊነት በድርጅትነቱ በኢሊኖይ ጠ/ግዛት የግብረሰናይ ድርጅቶች ደንብ መሠረት የተመዘገበ ነው። የድርጅቱ አድራሻ ችካጎ ከተማ (አሜሪካ) ነው።

### 1.2. ህጋዊ ሰውነት

ሀ. ኢትዮጵያዊነት ለበጎ ሥራ፤ ለትምህርታዊና ለሳይንሳዊ ተግባራት በአሜሪካን ዉስጥ-ገቢ መስሪያ ቤት (IRS) ደንብ በክፍል 501(c)(3) እና በተመሳሳይ የፌደራል ታክስ ህግ የተቋቋመ ግብረ-ሰናይ ድርጅት ነው።

ለ. ድርጅቱ በIRS አንቀጽ 501(c)(3) መሠረት ለተፈቀዱት አገልግሎቶች አቅራቢዎች ከሚአደርገው ህጋዊ ክፍያ በስተቀር ማናቸዉም የድርጅቱ ገቢ ለግለሰቦች፤ ማለት ለድርጅቱ አባሎች፤ወይም ዴሬክተሮች ወይም የባለአደራ ቦርድ የግል ጥቅም አይዉልም ወይም አይሰጥም። እንዲሁም የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ከመብት ጥያቄዎች አሻገር በማናቸዉም የፖለቲካ ፓርቲ የሚወክሉ ተወዳዳሪ ግለሰቦችንም ሆነ በስልጣን ላይ ያሉ የፖለቲካ ተመራጮችን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው። ይህ የተከለከለ ስልጣናዊ ድጋፍ ለፖለቲካ ወንበር ተፎካካሪዎችን የሚደግፉ ወይንም የሚነቅፉ ጽሁፎችን ማሳተምንና ማሰራጨትንም ያካትታል።

ሐ. በነዚህ የመተዳደሪያ አንቀጾች የተጠቀሱት አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ ድርጅት አንቀጽ 501(c)(3) የማይፍቅዳቸውን ሌሎች ተግባራትንም አይሰራም።

## አንቅጽ 2፡ አባልነት

2.1. ሁለት አይነት አባልነቶች ይፈቀዳሉ፡- ግለሰባዊና ድርጅታዊ (ልዩ)።

2.2. ግለሰባዊ አባልነት

ሀ. ማንም በትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነና እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ/ች ሰው "የዜጎች ቃልኪዳን ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ" የሚባለዉን ሰነድና በድርጅቱ የመተዳደርያ ደንብ የተጠቀሱትን ተልእኮ እስከተቀበለ/ች ድረስ እና የድርጅቱን ዓላማ በሚጻረር ድርጅት አባል እስካልሆነ ወይንም ተጻራሪ ድርጊቶችን እስካልፈጸመ ድረስ እዚህ ድርጅት በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል።

ለ. በተጨማሪ በወቅቱ የተደነገገዉን የመመዝገቢያና የአባልነት ክፍያ ይፈጽማል።

ሐ. ግዴታቸዉን ያሟሉ አባላት በማናቸዉም የድርጅቱ ተግባራት የመካፈል፤ በጠቅላላ ጉባኤ የመሳተፍ፤ የመምረጥ፡ የመመረጥና ሃላፊነትም የመያዝ ሙሉ መብት ይኖራቸዋል።

2.3. ልዩ (ድርጅታዊ) አባልነት

ሀ. (1) "የዜጎች ቃልኪዳን ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ"ን እንዲሁም የኢትዮጵያዊነትን ተልእኮ የተቀበለ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ ህዝባዊ ድርጅት (2) ድርጅቱን አፍርሶ ለመዎሃድ የማይችልበት ምክንያት በአሳማኝ መንገድ ያቀረበ ድርጅት ልዩ አባል ሊሆን ይፈቀድለታል።

ለ. ልዩ አባልነት የተሰጠው ድርጅት በጊዜው በስራ ላይ ያሉ ድርጅታዊ መመዝገቢያና አባልነት ክፍያዎችን በሙሉይከፍላል።

ሐ. የልዩ አባላት የድምጽ አሰጣጥ ሁኔታ በባለአደራዎች ቦርድ ይወሰናል።

መ. ማንም የልዩ አባል ወኪል በኢትዮያዊነት ውስጥ የምርጫ ቦታ ለመወዳደር አይችልም።

### 2.4. የስነ ምግባር መመሪያ

ለኢትዮጵያዊነት አባልነት ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር የስነምግባር መመሪያም ለፊርማ አብሮ ይቀርባል። የዚህ አስፈላጊነት የመላ አባላቱ ምግባርና ሥራ ከድርጅቱ መንፈስ ጋር ህብር እንዲሆን ስለሚረዳ ነው።

### 2.5. አባልነትን ስለማጣት

ሙሉ መብትን ለማስጠበቅ የአባልነት ክፍያ በጥር ወር ውስጥ መጠናቀቅ አለበት። እስከ አመቱ መጨረሻ የአባልነት ክፍያን አለማጠናቀቅ፣የአባልነት ስምምነቶችን መጣስ ወይንም የለየላቸው የስነምግባር ጥሰቶችን መፈጸም ከአባልነት ያስወግዳል። ከአባልነት የተወገዱ ሁሉ ይግባኛቸዉን ለባለአደራዎች ቦርድ ለማቅረብ መብት አላቸው።

## አንቀጽ 3፡ ድርጅታዊ መዋቅሮችና መሪዎች

3.1. ኢትዮጵያዊነት በነጻ የሚያገለግሉ አባላት የሚያካሂዷቸው ሁለት የስራ ክፍሎች ይኖሩታል።

ሀ. <u>የአማካሪዎች ቦርድ</u>፡- ክዚህ በሁዋላ “አማካሪዎች” በመባል የሚጠራ። ይህ አካል ስራው ማማከር ብቻ ሆኖ ከድርጅቱ ዉጪ የሆኑ ከ3 እስከ5 በተመክሮአቸዉና በስብእናቸው የተመሰገኑና የማናቸዉም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑ አዛዉንት አባላት ይኖሩታል። የአማካሪዎቹ ምርጫ በጠቅላላ ጉባኤው የሚጸድቅ ይሆናል።

ለ. <u>የዲሬክተሮች ቦርድ</u>፡-ክዚህ በሁዋላ “ዲሬክተሮች” በመባል ይጠራል። ዲሬክተሮቹ ከ11-15 አባላት ሆነው ማናቸዉም የአስተዳደር፣ የገንዘብና የስራ ማስፈጸም ሃላፊነት ይኖራቸዋል። ዲሬክተሮቹ የአባልነት ግዴታቸውን ባሟሉ አባላት የሚካሄድ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመርጣቸው ይሆናሉ። እነሱም ከመሃከላቸው ‘የስራ አስፈጻሚ ቡድን’ ማለትም ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ሂሳብ-ያዥ፣ ፀሃፊ፣ ሂሳብ-መርማሪ እና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በመምረጥ የድርጅቱን የዕለት ከዕለት ተግባራት እንዲከናወኑ ያደርጋሉ።

### 3.2. የአማካሪዎች አደረጃጀት

ሀ. የአማካሪዎች አባላት በዲሬክተሮች ተጠቁመው በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣሉ።

ለ. የአማካሪዎች የአገልግሎት ዘመን 3 ዓመታት ይሆናል።

ሐ. አማካሪዎቹ በመጀመሪያ ስብሰባቸው ሊቀመንበርና ፀሃፊ ይመርጣሉ።

መ. ስብሰባ መጥራትና ማካሄድ የሊቀመንበር ሃላፊነት ነው።

ሰ. ቃለ ጉባኤ መዉሰድ፤ እንዲሁም ቃለ ጉባኤዎችንና ሌሎች ተፈላጊ ሰበዶችን መመዝገብ መያዝ የጸሃፊ ሃላፊነት ነው።

## 3.3. የአማካሪዎች ስልጣንና ሃላፊነት

አማካሪዎች የሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-

ሀ. በዲሬክተሮች ላይ የሚቀርቡ ስሞታዎችንና በድርጅቱ ዉስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በመፍታት የድርጅቱ ደህነት ትጠብቆ ስራዉን እንዲአከናዉን መርዳት፤

ለ. የኢትዮጵያዊነት ታዋቂነት እንዲአድግ የሚረዱ አዳዲስ ዘዴዎችን ማፍለቅ፤ ድርጅቱን ለማደርጀት የሚረዱ የርዳታ ምንጮችን መጠቆምና መልካም የህዝብ ግንኙነት እንዲሰፋ መርዳት፤

ሐ. አማካሪዎቹ በአመት አንድ ጊዜ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከዚያም በላይ ስብሰባ ያደርጋሉ።

## 3.4. የዲሬክተሮች ቦርድ አደረጃጀት

ሀ. የዲሬክተሮች አገልግሎት ዘመን 2 ዓመታት ይሆናል።

ለ. ፕሬዚደንቱ የድርጅቱ ዋና የስራ አመራር ሃላፊ ሆኖ የዲሬክተሮቹ ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ማናችዉም የድርጅቱ ስራና ንብረት በተመደቡ ሃላፊዎች በሥርአት መካሄዳቸዉንና የድርጅቱ ንብረት መጠበቁን ይከታተላል። በተጨማሪም ፕሬዚደንቱ ድርጅቱን በማናቸዉም ህዝባዊ ድርጅት፤ በመንግስት፤ በአለም-አቀፍ ድርጅቶችና በፖለቲካ ፓርዎች ግንኙነት ወካይ ነው።

ሐ. ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፕሬዚዳንቱ በስራ በማይገኙበት ወቅት በወካይነት የፕሬዚደንቱን ተግባራት ሁሉ ያከናዉናል። እንዲሁም በተፈለገበት ቦታ ሁሉ ፕሬዚደንቱን ያግዛል።

መ. ጸሃፊው የድርጅቱን መዛግብት በሙሉ በሃላፊነት ይይዛል። እንዲሁም ኦፊሴል ግንኙነቶችና ዉሳኔዎችን እንዲሁም ዲሬክተሮን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን ይጠብቃል፣ይጠብቃል። እንደአስፈላጊነቱም የፕሬዚዳንቱ ወይንም የም/ፕሬዚዳንቱ ምትክ በመሆን ይሠራል።

ሰ. የገንዘብ ሃላፊው የሂሳብ ሰነዶችን ሁሉ ይይዛል፤ በዳይሬክተሮች ህጋዊ ፊርማ የተፈቀዱ የወጪ መረጃዎችንና አስፈላጊ የሂሳብ ሰነዶችን በመጠበቅ በአመት ሁለት ጊዜ የሂሳብ ሪፖርቶችን ያቀርባል። በማናቸዉም አስፈላጊ ሥራ ከሂሳብ ተቆጣጣሪው (ከኦዲተሩ) ጋር ይተባበራል።

ረ. ኦዲተሩ የድርጅቱን የሂሳብ አያያዝ በትክክል መካሂአዱን ቋሚና ህጋዊ በሆነ መንገድ ይቆጣጠራል፤ ሲጠየቅም ለዲሬክተሮች፡ ለአማካሪዎችና ለጠቅላላ ጉባኤውም ሪፖርት ያቀርባል።

ሠ. የአባላትና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው የአባላት ምልመላን፡ የህዝብ ግንኙነትንና ድርጅቱን የማስተዋወቅ ስራዎችን ይመራል።

ቀ. በኢሊኖይ ጠ/ግዛትህግ መሰረት አማካሪዎችና ዲሬክተሮች በኢትዮጵያዊነት ድርጅት ላይ ለሚቀርቡ ለማናቸዉም ክሶች ድርጅታዊ እንጂ የግል ተጠያቂነት የለባቸዉም። እንዲሁም አማካሪዎች ለኢትዮጵያዊነት በሚሰጡት አገልግሎት፤ ወይም በድርጅቱ ዉስጥ በሚይዙት የሃላፊነት ቦታ ምክንያት ከባለጉዳዮች ጋር በሚኖራቸው ንክኪ ወይም ግንኙነት ሳቢያ ጉዳት ደርሶብናል ብለው ስሞታ ወይም ክስ የሚአሰሙ ሰዎች ቢኖሩ አማካሪዎቹንብ ሆነ ዲሬክተሮችን በግል የሚያስጠይቅ አንድም ምክንያት አይኖርም።

ሸ. አንድ ዲሬክተር ከባድ ጥፋት መፈጸሙ በ5 ዲሬክተሮች ወይም በ10 የድርጅቱ አባላት ከማስረጃ ጋር ጠንካራ ክስ ከቀረበበት ጠቅላላ ጉባኤው በቂ ሆኖ ካገኘው ከቦታው ሊያነስው ይችላል።

## 3.5. የዲሬክተሮች ሃላፊነትና ስልጣን

የኢትዮጵያዊነት ዲሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት የጋራ ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ. የአጭርና የረጅም ጊዜ የስራ ፕላን፡ መርሃ-ግብርና በጀት አዘጋጅቶ እንዲሁም የአመቱን የስራ እንቅስቃሴ ዘገቦ ለጠቅላላ ጉባኤው ማቅረብ፤

ለ. በየቦታው የሚደራጁ የኢትዮጵያዊነት ቅርንጫፎችን ተቀብሎ የመደራጃና የድርጅት ማፍረሻ መመሪያዎችን አውጥቶ መስጠት፤

ሐ. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ማሰናበት፤

መ. የኢትዮጵያዊነት ዲሬክተሮችን እና ሠራተኞችን የሚመለከት ህግና መመሪያ ማዉጣት፤ ሰራተኞችን ለመቅጠር፤ ለማሰናበት፤ የገንዘብ አያያዝን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፤ ሂሳብን በትክክል ለመያዝና የህግ ባለሙያዎችህን አገልግሎት ለመጠቀም

እንዲሁም ድርጅቱን የማስተዋወቅ ስራዎችን በስርአት ለመምራት የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ማዉጣት፤

ሰ. ማናቸዉንም የኢትዮጵያዊነትን ህጋዊ ሰነዶች፣ ገቢና ወጪዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያዊነት አገልግሎት የተቀበሉ ወይም የሰጡ ሰዎችን ዝርዝር መያዝ፤

ረ. የምልመላና፤ ከህዝብ ጋር የመገናኛ ጽሑፎችን፤ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት። በተለይም በሃገር ዉስጥና ከሃገር ዉጪ የሚኖረዉን ኢትዮጵያዊ በሀገር ዉስጥ ስለሚካሄዱ የሰው ልጅ መብት ረገጣዎች የሚዘገቡበት እና እነሱንም ለመቋቋም መደረግ ስለሚገባቸዉ ክንውኖች ውይይትና ምክክር የሚካሄድበት ድህረ-ገጽ ተዘጋጅቶና በጥራት ተጠብቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

ሠ. ኢትዮጵያዊነት በለጋሾች፣ በክፍያ ውይም በስጦታ የሚአገኛቸውን ገንዘቦችና ወጪዎች በህጋዊና በከፍትኛ ደረጃ የሙያ አሰራር እንዲያዙ ማድረግ፤

ሸ. በኢትዮጵያዊነት ስም የባንክ ሒሳብ ቁጥር መክፈትና በተመደበ አንድ ዲሬክተርና በገንዘብ-ያዡ ሁለት ፊርማዎች እንዲካሄድ ማድረግ፤

ቀ. አግባብ ያለው የሂሳብና የንብረት አያያዝ ቁጥጥር ዘዴን መዘርጋት፤

በ. የስራ አመት በገባ በስድስተኛው ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብና በዓመቱ መጨረሻ ሙሉ የስራ ሪፖርትና የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ፤

ተ. ህግ የሚጠይቃቸውን የመንግስት ፎርሞችና ሪፖርቶች በጊዜው አሟልቶ ማስገባት፤

ቸ. የኢትዮጵያዊነትን ጠቅላላ ጉባኤና ሌሎች ኦፍፊሴላዊ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት፤

ኀ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የድርጅቱን ስራ ለመቆጣጠርና ጠቅላላ የድርጅቱንና የቅርንጫፎቹን ስራ የሚመለከቱ ዝርዝር የስራ መመሪያዎችን ማውጣት ናቸው።

## 3.6. ስብሰባዎች

ዲሬክተሮቹ ምድብና ልዩ ስብሰባዎችን እንደሁኔታው አመቺነት በቴሌኮንፈራንስ ጭምር ያካሂዳሉ።

### 3.7. ምልዓተ ጉባኤ

ከመቶ ሃምሳው ዲሬክተሮች ከተገኙ ማናቸዉንም የድርጅቱን ጉዳይ ለማካሄድ ምልዓተ ጉባኤ ተማልቷል።

### 3.8. ቀሪነት

ያለ ፈቃድ በአንድ የስራ አመት ሶስት ጊዜ ከስብሰባ የቀሩ የቦርድ አባላት ከዲሬክተርነት ቦታቸው እንዲለቁ ይደረጋል።

## አንቀጽ 4፡ ስብሰባዎች

### 4.1. ጊዜና ቦታ

ማናቸውም ስብሰባ ለአባላት አመቺ በሚሆን መንገድ ዲሬክተሮች በሚወስኑት ቦታና ጊዜ ይካሄዳል።

### 4.2. አመታዊ ጉባኤ

ጠቅላላ ጉባኤዉ በአመት አንድ ጊዜ ተሰብስቦ የድርጅቱን ዋና ዋና ክንዋኔዎችንና መርሃ-ግብርን፤ የሃላፊዎችን ምርጫና ማውረድን ያከናውናል። እንዲሁም ለጉባኤው ዉሳኔ በሚቀርቡ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ዉሳኔ ይሰጣል። እንደአስፈላጊነቱም ቅርንጫፎች በግለሰብና በልዩ አባላት ስም ድምጽ የሚሰጡ ወኪሎችን መሰየም ይፈቀድላቸዋል።

### 4.3. ልዩ ስብሰባዎች

ለተለያዩ አብይ ጉዳዮች ልዩ የአባላት ጉባኤዎችን ለመጥራት ዲሬክተሮች ወይም አማካሪዎች ውይም ከአባላት ሃያ በመቶ ከፈረሙ መጠየቅና ማስፈጸም ይችላሉ።

### 4.4. የአመታዊና የልዩ ስብሰባዎች ማስታወቂያ

የተለየ ህጋዊ መመሪያ ካልተሰጠ በስተቀር ማናቸዉም አመታዊ ወይም ልዩ ስብሰባ መጠራቱን የሚያበስር የጽሁፍ ማስታወቂያ የስብሰባውን በታና ጊዜ ገልጾ ይወጣል። ስብሰባው ልዩ ከሆነ የተጠራበት ምክንያትም ተገልጾ ለያንዳንዱ ድምጽ ሰጪ አባል ከስብሰባው ቢያንስ 15 ቀን ቢበዛ 60 ቀን ቀደም ብሎ መላክ አለበት።

### 4.5. ሰብሳቢ እና  የስብሰባ ሥርአት

ሀ.  የአባላት ጉባኤ በፕሬዚዳንቱ ወይም በምክትል ፕሬዚዳንቱ ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ለስብሰባው መሪነት በሰየመው ሰው ይመራል።  ጸሃፊዉ ወይም ሌላ የዲሬክተሮች ቦርድ የሰየመው አባል ቃለጉባኤ እንዲወስድና አግባብ ያላቸዉን ሰነዶች ለስብሰባው እንዲበትን እንዲሁም ከስብሰባው እንዲሰበስብ ይደረጋል።

ለ.  ስብሰባው "በሮበርትስ  የስብሰባ አመራር ሕግጋት" የመጨረሺያው እትም መመሪያነት የካሄዳል።

ሐ.  የጉባኤው ሊቀመንበር ካላሻሻለው በስተቀር የሚከተለው የስብሰባ ቅደም ተከተል ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡- (1) ስብሰባዉን በስርአት መክፈት (2) ምላተ ጉባኤ መኖሩን ማወጅ (3) ያለፈዉን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ማንበብና ማጽደቅ (4) በሃላፊዎች የሚቅርብ ሪፖርት ቢኖር ማቅረብ (5) ሌሎች በአጀንዳው የተጠቀሱ ጉዳዮች እንዲታዩ ማድረግና (6) ስብሰባዉን መዝጋት።

### 4.6. ምልዓተ ጉባኤ

በማናቸዉም ስብሰባ ከድርጅቱ አባላት በመቶ አርባው ከተገኙ  የድርጅቱን ጉዳዮች ለማካሄድ ምልዓተ ጉባኤ ይሟላል። ምልዓተ ጉባኤ ባይሟላ  ሁለተኛ ጉባኤ ለተመሳሳይ ጉዳይ ይጠራና ከድርጅቱ አባላት ከመቶ ሰላሳ ሶስት ከተገኙ ስብሰባው ይካሄዳል።

### 4.7. ድምጽ አሰጣጥ

ሀ.  ግዴታዉን ያሟላ ማናቸዉም አባል በየትኛውም ስብሰባ ድምጽ የመስጠት መብት አለው፤

ለ.  የድርጅቱ የስራ-አስኪያጅ ተመራጮች በድምጽ ብልጫ ይወሰናሉ/ይሞላሉ።

## አንቀጽ 5፡ ኮሚቴዎች

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጡት ዲሬክተሮች በመተዳደሪያ ደንቡ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት በድምጽ ብልጫ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን አስፈላጊ ሆኖ እንደታያቸው መሰየምይችላሉ። የኮሚቴዎችን የአገልግሎት ዘመንም ይወስናሉ። እንዲሁም ዲሬክተሮች በኮሚቴዎች ዉስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት፤ አባላትን ለመለውጥና ኮሚቴዎችን ለማፍረስ ሙሉ ስልጣን አላቸው።  ድርጊታቸዉንም ጠቅላላ ጉባኤዉ በሚሰበስብ ወቅት ከነምክንያቶችም ጭምር የማስረዳት ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 6፡ ጠቅላላ የአሰራር መመሪያዎችና መስፈርቶች

### 6.1. የሂሳብ አመት

የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት እ.አ.አ. ከጥር 1 እስከ ታህሳስ 31 ይሆናል።

### 6.2. ማህተም

የድርጅቱ ማህተም ቅርፅና ይዘት ዴሬክተሮቹ እንደሚዎስኑት ይሆናል።

## አንቀጽ 7፡ ደንብ ማሻሻልና ማፍረስ

ሙሉ የአባልነት ግዴታቸዉን በተወጡና ክፍያቸዉን ባሟሉ የድርጅቱ አባላት ከፍተኛ አብላጫ ድምጽ (ሁለት ሶስተኛ) ይህ መተዳደሪያ ደንብ ሊሻሻል ወይም ሊተካ ይችላል። ድርጅቱ እንዲፈርስ ከተወሰነ፤ ንብረቱ አንድ ወይም ሁለት ለሚሆኑ ከኢትዮጵያ ውስጥ ወይንም ውጭ የተመዘገቡ ህዝባዊ ድርጅቶች ይከፋፈላል። ተጠቃሚ የሆኑት ድርጅቶች ከኢትዮጵያዊነት ጋር ተቀራራቢ አላማ ያላቸዉ መሆን አለባቸው። በአሜሪካን አገር የተመዘገቡ ከሆኑም በሃገር ዉስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ደንብ ክፍል 501(c)(3) አተረጓጎም ከቀረጥ ነጻ የሆኑ መሆን ይኖርባቸዋል።

## አንቀጽ 8፡ በስራ ላይ የሚዉልበት ቀን

ደንቡ የጸደቀበት ቀን፡- ነኃሴ 7፤ 2004 ዓ.ም.

(Ratified: August 13, 2012).

። ። ። ። ።

Website: http://www.ethiopiawin.net